# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎች የምዝገባ ማስፈፀሚያ መመሪያ ቁጥር 6/2007

ጥቅምት 2007 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ማውጫ

| አርዕስት | ገጽ |
|---|---|
| 1. መግቢያ | 2 |
| 2. ክፍል አንድ (ጠቅላላ ድንጋጌ) | 3 |
| 3. ክፍል ሁለት (የምዝገባ መስፈርቶች) | 4 |
| 4. ክፍል ሶስት (የባንክ ሂሳብ አከፋፈትና የመሬት አቅርቦት) | 6 |
| 5. ክፍል አራት (ተግባርና ኃላፊነቶች) | 9 |
| 6. ክፍል አምስት (ልዩ ልዩ ጉዳዮች) | 11 |
| 7. ልዩ ልዩ ቅፃች | 14 |

City Government of Addis Ababa

6) ተመዝጋቢዎች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መንግስት በሚያወጣው ፕሮግራም መሠረት የጣት አሻራ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን ይገባቸዋል፤

7) በአፓርትመንት ቤት ግንባታውን ወጪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 መሠረት ሙሉ ክፍያ በውጭ ምንዛሪ ከፍለው በአገር ውስጥ በሚከፈተው የብር ሂሳብ ገቢ ያደረጉበትን የደረሰኝ ቅጂ ማቅረብ የሚችሉ፤

8) አፓርመንት ለመገንባት ከሚያስፈልገው ወጪ በግለሰብ ደረጃ የሚጠበቅበትን 50 በመቶ ክፍያ በምዝገባ ወቅት በሚኖሩበት ሀገር በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል የባንክ ሂሳብ በመክፈት የሚያስተምጥና መሬት ተዘጋጅቶ ለማህበሩ ሲረከብ የቀረውን 50 በመቶ ሙሉ በሙሉ በመክፈል የግንባታ ፍቃድ ለመውሰድ ዝግጁ የሆነ እና በውጭ ምንዛሪ ከፍለው በሀገር ውስጥ በሚከፈተው የብር ሂሳብ ገቢ ያደረጉበትን የደረሰኝ ቅጂ ማቅረብ የሚችሉ፤

9) ከዚህ በፊት በራሱም ሆነ በትዳር ጓደኛው ስም የመኖሪያ ቤትም ሆነ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በየትኛውም ክፍለ ከተማ የሌለው ወይም ኖሮት ለሶስተኛ ወገን ያላስተላለፈ፤

## 5. በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት የተደራጁ ቤት ፈላጊዎች

በዚህ ፕሮግራም መሳተፍ የሚፈልጉ ማህበራት፡

1) ከዚህ በፊት በራሱም ሆነ በትዳር ጓደኛው ስም በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በየትኛውም ክፍለ ከተማ የመኖሪያ ቤትም ሆነ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ የሌለው ወይም ኖሮት ለሶስተኛ ወገን ያላስተላለፈ፤

2) በመንግስት በተዘረጉት ሌሎች የቤት ልማት ፕሮግራሞች ላይ ተጠቃሚ ያልሆነ ወይም ለመጠቀም ያልተመዘገበ ወይም ተመዝግቦም ከሆነ ምዝገባውን መሠረዙን ወይም መተውን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፡

3) አንድ ማህበር በህጋዊ መንገድ በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር ለመመዝገብ የሚችለው ሁሉም የማህበሩ አባላት የተገመተውን የግንባታ ወጪ 50 በመቶ በውጭ ምንዛሬ መክፈል ሲችሉ ብቻ እና መሬት ተዘጋጅቶ ለማህበሩ ሲረከብ የቀሪውን 50 በመቶ ሙሉ በሙሉ በመክፈል የግንባታ ፍቃድ ለመውሰድ ዝግጁ የሆነ መሆናቸው ሲረጋገጥ ነው፡፡

4) ማህበሩ እንደተመሠረተ የሚቆጠረው የተገመተውን የግንባታውን ወጪ 50 በመቶ ክፍያ ፈጽሞ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፤

5) የነባር ማህበራትን አመዘጋገብ በተመለከተ ቀደም ሲል በተደራጁበት ወቅት የከፈሉት ክፍያ በ5(3) የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ ይመዘገባሉ። የማያሟላ ከሆነ ደግሞ የጎደለውን ገንዘብ ማሟላታቸውን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አቅርበው በሀገር ውስጥ፣ ዓለም አቀፍ ግንኙነትና የዳያስፖራ ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት በኩል ሲረጋገጥ የሚመዘገቡ ይሆናል።

6) ለነባር ማህበራት ነባር መሆናቸውን ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና ከማህበራት ማደራጃ ማረጋገጫ ሲያመጡ በሀገር ውስጥ፣ ዓለም አቀፍ ግንኙነትና የዳያስፖራ ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት በኩል ሲረጋገጥ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ይሆናል።

7) ሁሉም የህብረት ሥራ ማህበራት የራሳቸው መጠሪያ ሲኖራቸው ተመሳሳይ ስያሜ ያላቸው ማህበራት ሲያጋጥሙ ቅድሚያ የተመዘገበው ማህበር እንዲጠቀምበት ተደርጎ ሌላኛው ማህበር ሌላ መጠሪያ

22. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ጸድቆ ከወጣበት ከጥቅምት ፬ ቀን 2007ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ድሪባ ኩማ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ

5.2. ለመደራጀት በመረጥኩት አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በራሴ ወይም በትዳር ጓደኛዬ ስም የተመዘገበ የመኖሪያ ቤት ወይም የቤት መስሪያ ቦታ የሌለኝ እና ከዚህ በፊትም የነበረኝን በሽያጭ ወይም በስጦታ ለሶስተኛ ወገን ያላስተላለፍኩ እና በመንግስት በተዘረጉት የቤት ልማት ፕሮግራሞች ከዚህ በፊት ተጠቃሚ ያልሆንኩኝ መሆኑን፡

5.3. ለምዝገባ ብቁ የሚያደርገኝ የቤቱን ግንባታ 50 ፐርሰንት በምዝገባ ወቅት በዩሮ፣ ፓውንድ ወይም የአሜሪካ ዶላር በዝግ ሂሳብ ማስቀመጤን፣ ቀሪውን 50 በመቶ መሬት ተዘጋጅቶ የግንባታ ፍቃድ ሲሠጥ የማስቀምጥ መሆኑን፤

5.4. በምረከበው ቤት በጋራ ህንፃ ህግ መሠረት ለመተዳደር ፈቃደኛ መሆኔን፤

5.5. በዚህ ማመልከቻ ቅጽ የሞላሁትና የሰጠሁት ማረጋገጫ ሀሰተኛ ሆኖ ቢገኝ የምዝገባው ውል የሚፈርስ መሆኑንና ቤቱን ለሚመለከተው ለማስረከብ ወይም በከፍተኛ የሊዝ ዋጋ ታስቦ ክንቅጣቱ ለመክፈል የምስማማ መሆኑን፤

5.6. ወደፊት የሚጠየቁ መረጃዎችን ለምሳሌ የጣት አሻራና ሌሎች መረጃዎችን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኔን እንዲሁም

5.7. ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው ተጠሪ የቤቱን ጉዳይ ተከታትለው እንዲያስፈጽሙ የወከልኳቸውና የሞላሁት መረጃ ሀሰት ሆኖ ቢገኝ በህጉ መሠረት ተጠያቂ እንደምሆን በመስማማት ይህን ቅጽ የሞላሁ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የአመልካች ሙሉ ስም-----------------------------

ፊርማ -------------------------

ቀን ---------------------------

ማሳሰቢያ፦ ይህ ቅጽ በእያንዳንዱ በግል ተመዝጋቢዎች አማካኝነት ተሞልቶ የሚቀርብ ነው፡፡

ቅጽ 005

4.3 ለምዝገባ ብቁ የሚያደርገኝ የቤቱን ግንባታ 50 ፐርሰንት በምዝገባ ወቅት በዩሮ፣ ፓውንድ ወይም የአሜሪካ ዶላር በዝግ ሂሳብ ያስቀመጥኩ መሆኑን እና ቀሪውን 50 በመቶ መሬት ተዘጋጅቶ የግንባታ ፍቃድ ሲሰጥ የማስቀምጥ መሆኔን፣

4.4 በምረከበው ቤት በጋራ ህንፃ ህግ መሠረት ለመተዳደር ፈቃደኛ መሆኔን፣

4.5 በዚህ ማመልከቻ ቅጽ የሞላሁትና የሰጠሁት ማረጋገጫ ሀሰተኛ ሆኖ ቢገኝ የምዝገባው ውል የሚፈርስ መሆኑንና ቤቱን ለሚመለከተው ለማስረከብ ወይም በከፍተኛ የሊዝ ዋጋ ታስቦ ክንትሜቱ ለመክፈል የምስማማ መሆኑን፣

4.6 ወደፊት የሚጠየቁ መረጃዎችን ለምሳሌ የጣት አሻራና ሌሎች መረጃዎችን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኔን እንዲሁም

4.7 በተ.ቁ 1 ላይ በተገለጸው የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ስም ከሌሎች የማህበሩ አባላት ጋር በፈቃደኝነት ለመደራጀትና የመኖሪያ ቤት ለመስራት የሚያስፈልገውን ቅድመ ሁኔታና መስፈርቶች በአዋጁና በመመሪያው መሰረት ያማላሁ በመሆኑ የህብረት ስራ ማህበሩ በአባልነት እንዲቀበለኝና ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው ተጠሪ የቤቱን ጉዳይ ተከታትለው እንዲያስፈጽሙ የወከልኳቸውና የሞላሁት መረጃ ሀሰት ሆኖ ቢገኝ በህጉ መሠረት ተጠያቂ እንደምሆን በመስማማት ይህን ቅጽ የሞላሁ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የህ/ስ/ማ/አባሉ ሙሉ ስም-------------------------------

ፊርማ ----------------------------

ቀን ------------------------------

ማሳሰቢያ፡- ይህ ቅጽ በእያንዳንዱ የህ/ስ/ማህበሩ አባል አማካኝነት ተሞልቶ የሚቀርብ ነው